# <u>አሳሳቢውን የትምህርት ስርዓት ዝቅጠት በኢሮብ ወረዳ ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?</u>

ክፍል ሁለት

## <u>ለምን ወጣቶቻችን በአካል በዓሊተና እየኖሩ ስለ ባእድ-አገር ያልማሉ?</u>

ከበየነ ገብራይ ደንማርክ፣

*በክፍል አንድ መጣጥፌ፣ "የአቶ ዚያደ ኃይሉ አጭር መልእክት ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ያለው የትምህርት ስርዓት ገና ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ ችግር ያለበት መሆኑን በግልጽ ለመገንዘብ ያስችለናል። በመሆኑም፤ እኔ ትምህርትን በተመለከተ በወረዳችን ዛሬ ያለው ችግር የተወሰኑ ተማሪዎች ችግርን በመፍታት ሊቀረፍ የሚችል አይደለም እላለሁ። ስለሆነም በኢሮብ ወረዳ ያለውን መሰረታዊ የትምህርት ባለድርሻዎችን ሁሉ ባካተተ መልኩ ጥልቅ ውይይት ተደርጎበት አጠቃላይ መፍትሔ ፍለጋ ላይ መተኰር አለበት እላለሁ። ሰረቱ በሚገባ በባለሙያዎች ተገምግሞ፣ ባለድርሻዎችን ሁሉ ባካተተ መልኩ ጥልቅ ውይይት ተደርጎበት አጠቃላይ መሰረታዊ መፍትሄ ፍለጋ ላይ መተኮር አለበት እላለሁ። ለዚህም፣ አሁን ያሉንን የተለያዩ የመወያያ መድረኮችን በመጠቀም፣ በአካል ልንገናኝ የምንችልም በአካል በመገናኘት በዚህ ጉዳይ ላይ ጥልቅ ውይይት ማድረግ ተገቢ ይሆናል"።* ብዬ ነበር የዘጋሁት። ዛሬም ዝምታ ወይም የተወሰኑ ጥቂት ተማሪዎችን ለመርዳት በሚደረገው እንቅስቃሴ አሁን በወረዳው ሰፍኖ ያለው የትምህርት ስርዓቱ ችግር ስለማይፈታ፣ ችግሩን ከመሰረቱ ለመቅረፍ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የጋራ ርብርብ ስለሚያስፈልግ፣ ይህን ዓይነንት መንገድና አሰራር ሊፈቅድ የሚያስችል አስተሳሰብን መሰረት ባደረገ መልኩ በጉዳዩ ላይ በግልጽ እንወያይ፣ የመፍትሄ ሃሳቦች እናመንጭ፣ ለመሰረታዊ መፍትሄው ፍለጋ ደግሞ በአንድነንት ለመስራት እንዘጋጅ እላለሁ።

ለዛሬው መጣጥፌ፣ ለምን ወጣቶቻችን በአካል በዓሊተና እየኖሩ ስለ ባዕድ ሀገር ያልማሉ? በማለት እንደ ርእስ ላስቀመጥኩት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ከመሞከሬ በፊት ኢሮቦች ከመቼ ጀምረው ነው መሰደድ የጀመሩት? የሚለውን ጥያቄ ለውይይታችን በመንደርደሪያነት ይረዳ ዘንድ ትንሽ ጠቀስ አድርጌ ልለፍ። በኔ ዕድሜ ያላችሁ ወገኖች ልታስታውሱት እንደምትችሉት በወጣትነታችን ጊዜ በኢሮቦች ዘንድ ዛሬ የምንታዘበው ዓይነት ስደት በዓይነትም ሆነ ስፋትና ጥልቀት ፈጽሞ የሚታሰብ አልነበረም። በኔ የወጣትነት ዘመን ኢሮቦች ከቀያቸው ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ይሄዱ የነበረው በትምህርትና በስራ ምክንያት ነበር። ከዚህ ውጭ ያለው የኢሮብ ህዝብ ወደ ሩቅ የባዕድ ሀገር መሰደድ ይቅርና በአከባቢው እንኳን ለስራ ፍለጋ የመወጡት በጣት የሚቆጠሩ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ።

የኢሮቦች ከአከባቢያቸው ራቅ ብሎ በዛ ባለ ቁጥር መሰደድ የሚጀምረው ከ1960ዎቹ ጀምሮ ሲሆን፣ በተለይ በደርግ አገዛዝ ዘመን በ1970ዎቹ ውስጥ ስደቱ በተወሰነ ደረጃ ሰፋ ብሎ ቀጠለ። የተወሰኑ ተማሪዎች የደርግን ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ግዳጅን በመሸሽ መሰደድ ጀመሩ።ከዚህ በተጨማሪም የተወሰኑ ወጣቶችም ለስራ ፍለጋ ወደ ዓረብ ሀገራት በተለይ ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ በርከት ባለ ቁጥር ተሰደዋል። ከዚህ ውጭ በራሱ አረመኔያዊ አገዛዝ በነበረው የደረግ አገዛዝ ዘመን እነኳን የኢሮቦች ስደት እንደ ዛሬ የበዛና የከፋ አልነበረም።

የኢሮብ ወጣቶች በብዛት መሰደድ የተጀመረውና እስካሁንም ሳያባራ እየቀጠለ ያለው በዚህ ባሳለፍናቸው 20 የኢህአዴግ አገዛዝ ዘመናት መሆኑ ሁላችን የምናውቀው ሃቅ ነው። የተሰደዱት ወጣቶች ጉዳይ እንዳለ ሆኖ አቶ ዚያደ ኃይሉ እንዳሉት ዛሬ በሀገር-ቤት ቀርተው ያሉት ወጣቶችም በአካል በኢሮብ እየኖሩ ህልማቸው ስለ ባዕድ ሀገር ኑሮ ሆኖ ነው ያለው። ስለዚህ የነዚህ ወጣቶች

በአካል በኢሮብ እየኖሩ ስለ ባዕድ ሃገር ማለም ለማስቆም ከተፈለገ፣ የወጣቶቻችን ችግር ከመሰረቱ ለመቅረፍና በስደት መንገላታታቸውን ለማስቀረት ከተፈለገ፣ ስለ ባዕድ ሀገር ያላቸው ህልምን አቁመው ስለ አከባቢያቸው ልማትና ዕድገት እንዲያስቡ ከተፈለገ፣ መተኮር ያለበት በቁንጽል በጣት የሚቆጠሩ ወጣቶች ችግር ለመቅረፍ ባለመ መፍትሄ ፍለጋ ላይ ሳይሆን የወጣቶቹን ችግር ከመሰረቱ በትክክል ታውቆ አጠቃላይ መፍትሄ ፍለጋ ላይ ባተኮረ መንገድ ነው ማሰብም ሆነ መሰራት ያለበት እላለሁ።

አጠቃላይ የኢሮብ ወጣቶች ስደት አጀማመርና ዛሬ የደረሰበት ደረጃ መድረስ በኔ እይታ ከላይ ባጭሩ እንደተቀመጠው ሆኖ፣ ለምንድን ነው ከኢሮብ ወረዳ እስከ ዛሬ ያልተሰደዱ ወጣቶች በአካል ኢሮብ እየኖሩ ህልማቸው ሁሉ ስለ ባዕድ ሀገር ሊሆን የቻለው? የሚለውን የአቶ ዚያደ ጥያቄ፣ በበኩሌ አንድ ሰው ምን ሲሆን ነው መፈጠሪያ ቀየውን ጠልቶ ስለ ባዕድ ሀገር ለማለም የሚገደደው? በሚለው በመተካት እሳቸው ከጠቀሷቸው 300 ተማሪዎች አንጻር ጥያቄውን ለመዳሰስና ለመመለስ እሞክራለሁ።

በአቶ ዚያደ ኃይሉ አጭር የእንግሊዝኛ መልእክት ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው 300 ተማሪዎች ለ10ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ተቀምጠው ፈተናውን ለማለፍ የቻሉት 39 ብቻ ናቸው። በተጨማሪም ከነዚህ 39ኙ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ያለፉት ደግሞ 7 ብቻ ናቸው። በዚህ ስሌት መሰረት ከ300 ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል የሚያስችል ነጥብ ያገኙት 7 ብቻ ናቸው። 293 ተማሪዎች ግን ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጥል ሚያስችል ነጥብ ለማምጣት አልቻሉም፣ ስለሆነም ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል አይችሉም ማለት ነው። እስቲ አሁን በነዚህ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናቸውን ለማለፍ ባልቻሉ 293 ተማሪዎች ላይ ብቻ በማተኮር እያንዳንዳችን ቀጥለው የተቀመጡ ጥያቄዎችን ራሳችንን በመጠየቅ ለመመለስ እንሞክር።

1. እነዚህ 293 ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ለማለፍ ያልቻሉበት ምክንያት ምንድን ነው? ተማሪዎቹ ሰነፍ ስለሆኑ፣ ብቃት ያላቸው አስተማሪዎች ስላላገኙ፣ ለትምህረት አስፈላጊ የሆኑ በቂ መጻህፍትና ማተሪያሎች ስላጡ፣ ወይስ ሌላ?
2. የነዚህ ከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ያልቻሉ 293 ተማሪዎች እጣ ፋንታ ምን ሆነ? ነጥባቸውን ለማሻሻል ትምህርት ለመቀጠል የምችሉበት ዕድል አገኙ? ዕድሉን ካለገኙስ ለምን? አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?.......ወዘተ.
3. እነዚህ 293 ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ነጥባቸውን ለማሻሻል ዕድል ካላገኙ፣ በአከባቢያቸው ሰርተው ራሳቸውን ችለው ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ እስካልተፈጠረላቸው ድረስ ምን ሊያደርጉ ወይም ሊያልሙ ይችላሉ?

ለውይይት መንደርደሪያነት ይረዳ ዘንድ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸውን የተወሰኑ ሃሳቦችን ባጭሩ ላስቀምጥ። እነዚህ 293 በሙሉ ሰነፍ ተማሪዎች ስለሆኑ ነው ፈተናውን ለማለፍ ያልቻሉት የሚለው አባባል አያስከድም። ስለሆነም ለነዚህ 293 ተማሪዎች 10ኛ ሆነ 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ለማለፍ ያልቻሉበት ሌላ ምክንያት መፈልግ የግድ ነው። እንደኔ እምንት ከነዚህ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ፈተናውን ለማለፍ እንዳይችሉ ካስቻሉዋቸው ምክንያቶች ውስጥ፣ ብቃት ያላቸው አስተማሪዎች እጥረት፣ ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ መጻህፍትና ሌሎች ግብአቶች ጉድለት.... የመሳሰሉት በግንባር ቀደም ሊቀመጡ ከምችሉ ምክንያቶች ውስጥ ዋናዎቹ ናቸው እላለሁ። እናንተስ ምን ትላላችሁ?

የነዚህ 293 ተማሪዎች ዕጣ ፋንታ ምን ሆነ፣ የት ደረሱ፣ የሚለው ጥያቄ በትክክል በመረጃ አስደግፋችሁ በዝርዝር መመለስ የምትችሉ እቦታው (ኢሮብ) ያላችሁ ወገኖች ስለሆናችሁ ዝርዝሩን

ለናንተ እተወዋለሁ። በርግጠኝነት ግን ከነዚህ ወጣቶች ውስጥ የተወሰኑት መረን የለቀቀ ድህነትን ለመሸሽና ሥራ ፍለጋ ወደተለያየ አቅጣጫ ተሰደው ሊሆኑ እንደሚችሉ መናገር የሚቻል ይመስለኛል። በተጨማሪም እነዚህ ወጣቶች ለወደፊቱ ሊታይ የምችል ብሩህ ተስፋ የሚሰጣቸው ሁኔታ በአከባቢው እስከሌለ፣ በአከባቢው ሰፍኖ ያለወ በማንኛው ሰዓት ሊፈናዳ የምችለው የጦርነት ድባብ እስካልተወገደ ድረስ የኢሮብ ወጣቶች በአካል ኢሮብ መሬት ላይ እየኖሩ ህልማቸው ስለ ባዕድ ሀገር መሆን ለወደፊተም ብሶበት ሊቀጥል እንደምችል ለሁላችን ግልጽ ሊሆን ይገባል።

ስለሆነም፣ በያንዳንዳችን ጉዳዩ ያሳስበናል፣ ይመለከተናል የምንል ወገኖች መመለስ ያለበት መሰረታዊ ጥያቄ፣ ወጣቶቻችን ስለባዕድ ሀገር ያላቸው የተሳሳተ ህልም አቁመው፣ ህልማቸው ስለ አከባቢያቸው ልማትና ብልጽግና እንዲሆን፣ አሁን በተማሪዎችም ሆነ በሌሎች እየታየ ያለውን ስደት ለማስቀረት፣ እኛ ኢሮቦች እንደ ማህበረሰብ፣ በአከባበው ያሉ የሃይማኖት ሆነ በጎ አድራጊ ድርጅቶች እንደ ድርጅት፣ መንግስት እንደ መንግስት በየፊናቸው ምን ማድረግ አለባቸው የሚለው ይሆናል።

አሁን ውይይታችን በወረዳው ስላለው የትምህርት ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት በሚለው አጀንዳ ላይ ብቻ ያተኮረ ስለሆነ፣ ሌላውን አጠቃላይ የወጣቶቻችን ችግሮች ለይደር አስቀምጠን በወረዳችን ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጥ እኛ ኢሮቦች እንደ ብሄረሰብ ትምህርትን በተመለከተ በምናደርጋቸው እርዳታዎች ሆነ የምናቀርባቸው ሃሳቦች ምን ላይ ያተኩሩ ይሁኑ? በሚለው ውይይቱን እንቀጥል።

በክፍል ሶስት ኢሮቦች እንደ ብሄረሰብ፣ በአከባበው ያሉት የሃይማኖት ሆነ በጎ አድራጊ ድርጅቶች እንደ በጎ አድራጊ ድርጅቶች፣ መንግስት ደግሞ እንደ መንግስት ትምህርትን በተመለከተ ምን ማድረግ አለባቸው፣ የሚሉትን ነጥቦች በቀደም ተከተል ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

በቀጣዩ ርእስ እስከምንገናኝ በያላችሁበት በቸር ሰንብቱ!